# ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?

ክፍል 3

ውሸታም ሰው ማስታወሻው ጣቃ ነው ተብሏል፡፡ የውሸታሞች መንጋ በኢሕአፓ ላይ ከተሰማራ ውሎ አድሯል፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ ነጋ ጠባ እነዚህ ቀጣፊዎች ይህን ድርጅት የለም ሞቷል፤ተኗል ጠፍቷል እያሉ በዚያው አፍ ደግሞ ቁም ስቅሉን ሲያሳዩትና ሲሰድቡት መደመጡ ነው፡፡ ጠላቶች ሲዋሹና ሲዘምቱበት በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ድርጅት አባል ነበርን ባዮች ግን በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ በደል የፈፀሙ በታኞችና አንጃዎች ደግሞ ቅሌታቸውና ክህደታቸውን የሸፈኑና ያለዘቡ እየመሰላቸው ኢሕአፓን በተመለከተ በየመድረኩ ይዋሻሉ፡፡ ኢሕአፓ ለነዚህ ውሸቶች ሁሉ መልስ በመስጠት ጊዜን ማጥፋት አለብኝ የሚል ባይሆንም አዲሱ ትውልድና ሌሎ ችም በሀሰቱ ጎርፍ እንዳይወሰዱ በየጊዜው እርምትና ማስተካከያዎችን ማድረግ፤ ውሸታሞችን ውሸታም ማለት ይገደዳል፡፡ ለምን ይዋሻል? የሚለውም ለዚህ ነው፡፡

ኢሕአፓ በሀገሪቷ የመጀመሪያው የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ ሲመሰረት ከምስረታው ጀምሮ የተመክሮ ድክመቱን ለማመንና ለማስተካከል በመጣር ረገድ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ጨቋኝ ስርዓ ቶችን ታግሎ ለውድቀታቸው የበኩሉን አስተዋፅዖ በማድረጉ ይኮራል እንጂ አይፀፀትም፡፡ ዛሬ ለአፄው ስርዓት ናፍቆት ያላቸው አላዋቂዎችና የያኔ ተጠቃሚዎች ወይም ታሪክ መማር ያለባቸ ው ግለሰቦች ቢኖሩም 85 በመቶ ሕዝብን ጢሰኛና ገባር አድርጎ፤ ዴሞክራሲን አጥፍቶ የቆየን ስርዓት ታግሎ መጣል ብሔራዊ ግዴታ ነበርና ይህንንም ኢሕአፓ በሽልም ተወጥቶታል፡፡ ድርጅቱ መቸምና ምንም ጊዜ ጥፋቶቹን አላመነም ብለው የሚቀላምዱ ግን ተራ ውሸታሞች ከመሆን የሚያመልጡበት ሁኔታ የለም፡፡ የሚታገል ድርጅት፤ ህያው የሆነ ሰው ስህተት መፈፀማቸው አይቀርም፡፡ ሁሉን አውቆና ከስህተት ርቆ ከውልደት እስከሞቱ የሚደርስ ፍጡር የለም፡፡ ኢሕአፓ ለሀገር ክብርና ለሰፊው ሕዝብ መበት ሲታገል በትግሉ ሂደት ትምህርትን እየገ በየና ከስህተቱም እየተማረ የጀግንነትን ታሪክ ፅፏል፡፡ የቁጭ አንበሶችና የሶፋ ፋኖዎችን ተከት ሎ ትግልን በአፉ እየቆላ ከተግባርም ርቆ፤ ከመስዋዕትነትም ሸሽቶ የሀፍረትና የፍርሀትን ታሪክ ፅፎ ሀገርና ሕዝብን አላሳፈረም፡፡ ዛሬ ሁሌም ትክክል ሊሆን የሚችለውን የኋላ መብራትን ሲያበ ራ ደግሞ ያኔ እንዲህ ባደረግኩ ኖሮ፤ ይህን ባልሰራሁ ኖሮ ብሎ ማሰቡ መቆጨቱ የማይቀር ነው፡ ፡ ያለፈው አለፈ ብሎም ነገሮችን አድበሰብሶ አላላፈም፡፡ ከፋሺስቶቹ ቀይ ሽብርና ከጠባቦቹም የተባባረ ጦርነትና ጥቃት በኋላም የድርጅቱ አመራር ባደረገው አራተኛ ጠቅላላ የአመራር ጉባዔው እስከዚያም (1972 ዓ.ም.) ያሳላፈውን ተመክሮ ገምግሞ ስህተቶቹንም አውጥቶ ተችቶባ ቸዋል፡፡ በ1976 በቋራ ባካሄደውም. ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔው ተመሳሳይ ግምገማን አድርጓል፡፡ የመድብለ ፓርቲን ስርዓት በመደገፍ፤ መሬት ለአራሹን በማስቀደምና የብሄረሰብ ጥያቄ በዴሞ ክራሲና የሀገርን አንድነት በጠበቀ ራስ አገዛዝ ክልል ይፈታ በማለት ወዘተ ተገቢውንም የፕሮግ ራም ለውጦች አደርጓል፡፡ በዚህ ወቅት ወያኔ በድንገት ተዓምር ተገለጠልኝ፤ የአልባኒያ ደቀመዝ

ሙር የቀላሁ ኮሚኒስት ነኝ እያለ ይቧርቅ አንደነበር መጥቀስም ያስፈልጋል፡፡የድርጅቱ ተቋሞች ና ራሱ ድርጅቱ በአጠቃላይም ባካሄዷቸው ስብሰባዎችና ጉባዔዎች ሁሌም ተመክሮን እያነሱ መገምገም ልምዳቸው በመሆኑ ስህተቶቹ እየተወገዱ ድርጅቱም ህልውናውን እየጠበቀና አፍራሾ ችን እያገለለና እየተቋቋመ ለመቀጠል ችሏል፡፡

ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ እንደገለፀው አድህሪ አገዛዞችን በመታገሉ ከማንም ይቅርታ አይጠይቅ ም፡፡ ሕዝበዊ ግዴታውን በመወጣቱ ይኮራል አንጂ፡፡ የሕዝብን ድል ነጥቆ በስልጣን የተሰየመውን የምርጥ መኮንኖች ቡድን በሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ተቃውሞ ታግሎታል፡፡ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት መኮንኖቹና ወታደሮቹንም የጨመረ፣ ሁሉንም ሀገር ወዳድ ድርጅት ያቀፈና ሰፊ መሰረት ያለው-- እንዲቋቋም ጠይቆ ነበር፡፡ ኅዳር 14 ቀን 1968 ዓ/ም. ባወጣውም ዴሞክራሲያ እትሙም ለምን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አስፈለገ በሚል ርዕስ በሰፊው አስረድቷል፡፡ ደርጉ ይህን በመቃወምና ስልጣንን በብቸኝነት በሕዝብ ላይ ለመያዝ በመወሰን ኢሕአፓን በፖለቲካው ሳይሆን በሀይል ሊያጠፋ ቆርጦ ተነሳ፡፡ በዚህም የጦርነት ዘመቻው የአድርባይ ምሁራን ቡድኖች ተባባሩት፡፡ ኢሕአፓም ትግሉን አፋፋመ እንጂ ግንባሩን አላጠፈም፡፡ ኢሕአፓ ሕዝብን አደራጅ ቶና መርቶ በደርግ ላይ በማስነሳቱና ሕዝባዊ ትግሉን በማጧጧፉ ከማንም ይቅርታን አይጠይቅ ም--ብሔራዊ ግዳጁን በመወጣቱ ይኮራል እንጂ! ፋሺስቱ ደርግም ኢሕአፓን ለማጥፋት ነፍሰ ገዳይ ሻለቆቹንና ወታደሮቹን ሲያሰማራና በገፍ ግድያ ሲያካሂድ፣ በመስከረም 2 በይፋ ጦርነትን አውጆ የኢሕአፓ አባላትን ሲገድልና ድርጅቱንም ሊያጠፋ ሲነሳ ኢሕአፓ የራስ መከላከል እርምጃን ለመውሰድ መነሳቱ ትክክል ነበር/ ነውም ብሎ ኢሕአፓ ያምናል፡፡ከአጥፊ አገዛዝ ራሱ ን የማይከላከል ማንም ሰው ራሱን ለጥቃት ሰለባ ያደርጋል እንጂ ሌላ ውጤት አያመጣም፡፡ ይህ የራስ መከላከል እርምጃ ቀስ በቀስ አቅጣጫውን ስቶ፣ በውሱን ደረጃዎችም ስህተትም ተደርጓል፣ መቆም ሲገባም ባለመቆሙ ጉዳትን በማብዛቱ ኢሕአፓ ስህተት ተፈፅሟል ብሎ ተቀብሏል፡፡ ይህ ን ስህተት በተመለከተ ሊጠየቅ የሚገባው  በተለይ አንድ አመራር አባል የነበረ ግለሰብ ቢሆንም መላው አመራር ጥፋቱን ጥፋታችን ብሎ በ 1972 ተቀብሎ ግለ ሂስ አድርጓል፡፡ ደርግን በየከተ ማው ተጋፍጠው ለወደቁና ስቃይ ለተቀበሉት አባሎቹ ኢሕአፓ አድናቆቱን እያሰማ ያ ትግል መደረግ ያለበት ትግል ነበርና ሸከሙም መቀበላችን አይቀሬ ነው ብሎም ይገልፀዋል፡፡ ኢሕአፓ ምንም እንኳነ የጠባብ ብሔረተኞችን አደጋ በጊዜ በሚገባ በመረዳትና ለመከላከል በመነሳት በኩል ድክምት ነበረብኝ ብሎ ግለ ሂሰ ቢያደርግም ለሕዝብ የእኩልነት መብት በመታገሉና ትምክህትና ጭቆናን በመቃወሙ አጠፋሁ የሚለው ጭራሽ የለውም፡፡ የዚያን ትውልድ ቆራጥነት ና ሞት አይፈሬነት የሚያንፀባርቁ ድርጅቶች ዛሬ አብብው በነበር ወያኔ 19 ዓመት በሕዝብ ላይ ባልቀለደም ነበር ማለታችን አልቀረም፡፡

ኢሕአፓ ከዚያን ጊዜም በኋላ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ተመክሮውን እየገመገመ ደጉንና ስህተ ቱን እያወጣ ትግሉን በተሻሻለና በተሳካ ሁኔታ ለመቀጠል ሞክሯል፣ ቀጥሏልም፡፡ ድርጅቱን

ዴሞክራሲያዊ አይደለም ብለው የሚከሱት ስለ ዴሞክራሲ ግን ግንዛቤያቸው ገለባ የሆኑ ቢበዙ ም ኢሕአፓ ባለበት ሁኔታና ተጨባጭ የትግል ሜዳ ዴሞክራሲያዊ ልምድን ለማዳበር ሲጥር የቆየ ድርጅት ነው። ኢሕአፓ የወሬ ሳይሆን የትገል ድርጅት ነበርና (ነውናም) ዴሞክራሲያዊ ነቱ ካለበት የትግል ሁኔታና መስክ ጋር የተቆራኘ መሆኑ አልቀረም። ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ህገ ወጥ ተብሎ የሚጠቃ ድርጅት ነውና ኢሕአፓ ተዝረክርኮ ምስጢራዊና ሙያተኛ አሰራርን ሰርዞ ይፋ ሊወጣ የሚችል አልነበረም/አይደለም። ትግሉ ግድ የሚለው ማዕከላዊነት ነበረው፤ ዛሬ ም አለው። በህቡዕ የሚሰራ ደርጅት ነበር/ነውም። የተዝረከረኩ ለአገዛዞች ጥቃትና ምት ሁሌም ሰለባ ሆነዋል። በእርግጥ በየካቲትና ከዚያ በኋላ ከነበረው ህቡዓዊነት ለየት ባለ መልክ ዛሬ ድርጅ ቱ ህቡዓዊነቱ ቀንሷል ማለት ይቻላል። ይህ ቢባልም ግን ዛሬም ቢሆን በሀገር ቤት ያለው የድር ጅቱ መዋቅር ሰፊ ጥቃት ሊደርስበት የሚችልና የደረሰበትም በመሆኑ አሰራሩ ሙሉ በሙሉ ህቡዓዊ ነው። ለወያኔ ጥቃት ተጋልጦ ከባድ ጉዳት እንዳይደርስበት ማለት ነው። ከዚህ ባሻገር ግን ኢሕአፓ የአባላትን ዴሞክራሲያዊ መብት በተቻለው መጠን ያከበረ ለመሆኑ አንዳንድ ሀቆ ችን እንጥቀስ፤

- ዋና ዋና የድርጅቱ ውሳኔዎቹ የሚወሰኑት በመላ አባላቱ በብዙሀን ድምፅ ነው፤
- ድርጅቱ ስብሰባዎችና ጉባዔዎችን በማካሄድ ውሳኔዎችን በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ያሳልፋ ል፤
- የድርጅቱ መሪዎች በጉባዔ ይመረጣሉ፤ ከሁሉም በላይ የሆነ ጣዖት ሊቀመንበር ኢሕአፓ ኖሮት አያውቅም። የጋራ አመራር መርህን ይከተላል
- በድርጅቱ በአጠቃላይና በሰራዊቱ በተለይ በቃኝ ያለ ጓድ የስንብት መብቱ ይከበርለታል
- በሰራዊቱም ቢሆን የመብት አስጠባቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ የማንም አባል መብት አይደፈር ም ነበር፤
- ድርጅቱ ራሱን ለማረም የመጀመሪያው መሳሪያው ሂስና ግለሂስ ሆኖ ቆይቷል።
- ዴሞክራሲን ያወቀና ያከበረ በስራ የሚውል ህግና ደንብ አለው

ሀቁ ይነገር ከተባለ ኢሕአፓ በድርጅትም በሰራዊትም ደረጃ የዴሞክራሲን መከበር ጫና ሰጥቶና በተወሰነ ደረጃም ለቀቅተኛ ሆኖ በራሱ ላይ ጉዳቶችን አምጥቷል። ከባድ ጉዳት አድርሰው የከዱ ትን ዳግም ወደ ድርጅት መልሶ እስከ አመራርም አድርሶ እንደገና እንዲጎዱት ራሱን አጋልጧል --ለዚህና መሰል ስህተቶቹም ኢሕአፓ ግለሂሱን ወስዷል። ስህተቶችን ለማረም የዕርምት እንቅስ ቃሴ ማካሄዱ ትክክል ቢሆንም በትጥቅ ትግል መስክ መጠበቅ ያለበትን ዲሲፕሊንና ስርዓትም በተመለከተ ለቀቅተኛ በመሆኑ ስህተቶችን ፈፅሟል ። ከዚህ ሁሉ ተምሯል፤ወደፊትም ይማራል። ድርጅት የሰዎች ስብስብ ነውና የሰው ድክመት ነፀብራቅ መሆኑም የሚቀር አይደለም። ዋናው ጉዳይ ስህተቶችን ለመቀነስና ላለመድገም መጣርና ንቃተ ህሊናንም ማዳበር መሆኑ ዛሬ ለብዙዎ ቹ ግልፅ ባለመሆኑ በሕዝብ ትግል ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ሁላችንም እናውቃለን። ጥቆማም በስድብነት እየተወሰደ መማማር ከባድ ሆኖ አለ ።

በድርጅቱ ላይ ሀሰትን የሚነዙት ክፍሎች አንዱ ያዋጣቸው ወይም የሚሸጥላቸው የመሰላቸው ውሸት የድርጅቱ አመራር ሳይለወጥ ዘመን አልፏል የሚለው ከስ አይሉት ትችት ነው:: በደፈና ው ወጣቱ ተኪ ይሁን የሚል የአዛኝ ቅቤ አንጓች ልፈፋም አቡነ ዘበሰማያታቸው ሆኗል:: ወጣቱ ትውልድ ተኪ እንዲሆን ማድረስና ማዘጋጀት አስፈላጊ ለመሆኑ መንም ጥርጥር የለውም:: ኢሕአፓ ከዚህ አንፃር ወጣቶችን ዛሬም ቢሆን በወክንድ አደራጅቶ ሰንደቁን እንዲረከቡ እያመ ቻቸ ነው:: ከዚያ ባሻገር ግን ሀቁ ሲነገር ኢሕአፓ በየጉባዔው አመራሩን ቀይሯል፣ አድሷል::ይሰ ራሉ፣ ያስፈልጋሉ ያላቸውን ደግሞ አስቀጥሏል:: አመራር የነበሩና ከአመራር ወጥተው ቆይተው የተመለሱም አሉ:: ቁም ነገሩ የድርጅቱን መርህና ግብ በስራ ከማዋልና የአመራርን ሚና ከመወ ጣት አንፃር ግለሰቡ ይጠቅማል አይጠቅምም የሚለው ብቻ ነው:: በፅናታቸውና ሕዝባዊነታቸው ለአድርባዮች ሾክ የሆኑትን የኢሕአፓ መሪዎች ከቦታቸው ለማስወገድ ግን ይህ በሀሰት መሰረት እየተካሄደ ያለው ቅስቀሳ ፍሬ ቢስ ነው:: በተለይም ቀስቃሾቹ የእኛ መሪዎች የሚሏቸው በዕድ ሜ ከኢሕአፓዎቹ ሲነፃፀሩ በጣም የገፉ ናቸውና:: የድርጅት መሪዎች ሁኔታ በቅድሚያ የሚመ ለከተው አባላቱን መሆኑም መዘንጋት የለበትም:: ኢሕአፓ ህግና ደንቡን የማያከበሩና ጣያትነት ን የሚመኙትን የአመራር አባሎች ደግሞ በሚገባ በየጊዜው አስወግዷቸዋል::

መቻልን ነው አለመቻል ብሏል የሀገራችን አንጋፋው ገጣሚ ጋይሉ ገብረ ዮሐንስ :: መቻል የሌለ በትን መቻሉ ራስን ለባርነት ማስጎንበስ ነው:: ግፍና ጭቆናን፣ ዘረኝነትንና አምባገነንነትን መቻል ሳይሆን አለመቻልና መታገል ነው ከሰው ልጅ የሚጠበቀው:: በመሆኑም በደፈናው መቻቻልን ሰባኪዎች ሲመረመሩ አወቁም አላወቁ አድርባይነትንና እጅ መስጠትን አቀንቃኝ ናቸው::ኢሕአ ፓና መኢሶን ባለመቻቻላቸው ዕልቂት መጣ እያሉ መሰረተ ቢስ ልፈፋ የሚያሰሙት ክፍሎች በተለይም ከሚያወግዙትና ስህተት ካሉት ተምረው ራሳቸው ከክፍፍልና ንትርክ መዳኑ ያልቻሉ መሆናቸውን በቅድሚያ መጥቀስ ያስፈልጋል:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሕዝብ ላይ ለደረሰው ሽብርና ዕልቂት በቅድሚያና በዋናነት ተጠያቂ ፋሺስቱ ደርግና አገዛዙ መሆኑን ለመሸፋፈን የሚደረግ መሰሪ ጥረት ነው:: ምሁራን በመጣላታቸው ሽብር አልተከሰተም:: ሕዝብ ከደርግ ተጋጭቶ የተወሰኑ ምሁራን የደገፉት ወታደራዊ አገዛዝ በሕዝብ ላይ ሽብርን አወጀ አካሄደ እንጂ:: ይህን መሰረታዊ ሀቅ ለመሸፋፈን ወንጀለኞቹም ከህዲዎችም ዛሬም እያደረጉ ያለው ጥረ ት እርቃኑን ወጥቶ መወገዝ ያለበት ነው:: ዋናው ጥያቄ የኢሕአፓና መኢሶን መቻቻል አልነበረ ም--የደርጉን ወታደራዊ አገዛዝ መቀበል ወይም መቃወም እንጂ:: ወደ ቁም ነገሩና ሀቁ ስንመጣ ደግሞ ኢሕአፓና መኢሶን የተለያዩት ዛሬ በተወሰኑ ድርጅቶች እንደምናየው በእንቶ ፈንቶ ሳይ ሆን በመሰረታዊ ጥያቄዎች የተነሳ ነበር:: ልዩነታቸውን ለማርገብ በአዲስ አበባ በምስጢር ሁለቱ ድርጅቶች በአመራር ደረጃ ተወያይተውም መኢሶን ወታደራዊውን አገዛዝ ሂሳዊ ድጋፍ መስጠ ት አለብን ሲል ኢሕአፓ ደግሞ ይህን በመቃወም ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም በሚል ም ትግሉ መቀጥል አለበት በማለቱ ሳይስማሙ ቀሩ:: ዛሬ ወያኔን እንደግፍ የሚል ድርጅትና ና ወያኔ ይውደም የሚል ድርጅት ይቻቻሉ ተብሎ ሰበካ ለመሆኑ አሳፋሪ መሆኑ ግልፅ አይደለ ም? ይህ የመኢሶንና የኢሕአፓ ልዩነት በመሰረቱ የኢሕአፓና የሕዝብ በአንድ በኩልና

የወታደራዊው ቡድን በሌላ በኩል የነበረ ልዩነት በመሆኑ ሊረግብ አልቻለም። ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አለገደብ ሲል የዴሞክራሲን መገደበ ያቀነቀነው የመኮንኖቹ አገዛዝና እነ መኢሶን ያቀረቡት መፈክር ለነቃ ለተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ የሚል ነበር። የሕዝብን መደራጀትና መታጠቅ ማን ተቃውሞ? ግና ዋናው አንገብጋቢ ጥያቄ ይህ አልነበረም። ሂደቱ ወደ አፈናና ጦርነትም የተሸጋገረው በኢሕአፓ ሳይሆን በአገዛዙና በምሁሮቹ ደጋፊዎቹ ለመሆኑ ዛሬ ሊደበቅ የሚችል አይደለም። መኢሶን በነፃው እርምጃና በፍጅቱ ግንባር ቀደም ሚና ነበረው። ከደርግም ጋር ሲጣላ ባወጣው መግለጫ ለጠቡ አንዱ ዋነኛ ምክንያቱ ደርግ ነፃ አርምጃን በኢሕአፓ ሳይ አላፋፍም በማለቱ ነው ብሎ በግልፅ በልሳኑ አስፍሮታል። የመኢሶንን ሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 67 (ሐምሌ 15/1970) ስንጠቅስ መኢሶን ከህብረቱ ስለመውጣቱ በሚል ምንያቶቹን ሲዘረዝር በገፅ 23 የሚከተለውን አስፍሯል፣

" ሐ / 1. በህዝባዊ ነፃ አርምጃዎች ለይ የተደረገው እገዳ እንዲነሳ፣ተፋፍሞ ያለማቋረጥ እንዲቀጥል እንዲደረግ፣

2. የተቋረጠው የሰፊው ሕዝብ መታጠቅ እንዲቀጥል

3. <u>በታወቁ የኢሕአፓ ቅጥረኛ ነፍስ ገዳዮች ላይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ</u>

4/ ቅጥር ነፍስ ገዳዮችን እያሰሩ መልቀቅ እንዲቆም "

ብንል ደርጉ አልሰማን አለ ብሎ መኢሶን አማሯል። መኢሶን ይህን አቅዋም ማለትም ግድያን ተገቢ ነው ብሎ ደርግን በለቀቅተኝነት እየከሰሰ ያለ መሆኑ ስለ ይዘቱና አቅጣጫው በቂ ጥቆማ ይሰጣል። መቻቻል የሚቻል አልነበረም። በፖለቲካው መስክ የተሸነፉት ደግሞ ጦርነት አውጀው ፍጅትን ሲያካሂዱ መከላከል ሀጢያትና ጥፋት ሊሆን አይችልም። ዛሬም ቢሆን አስከፊን የወያኔ አገዛዝ ለመገርሰስ ብረት አንስቶ መታገልና መስዋዕትነትንም መክፈል የግድ ነው። አናልቅም አንሞትም ከተባለ ሀገር ከዘረኞች አትላቀቅም። ዕድላችን ሆኖ ደግሞ መስዋዕትን የማይጠይቅ ሀገር አድን ትግል ገና አልተከሰተም !! ስለዚህም ትግል ሲፋፋም የሚጠይቀውን መስዋዕትነት በሕዝብ ማስጨረሰ ፈርጀው እጅ መስጠትንና አንገት መድፋትን የሚሰብኩ የትግልና የሀገር ጠር ናቸው። ስለዚህም በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በመሸፋፈንና በውሸት በመደበቅ ኢሕአፓ መቻቻልን ተቃወመ፣ የጦርነትን መንገድ ቀድሞ ተጓዘ ወዘተ የሚሉት ክሶች መሰረተ ቢስ ውሸቶች ናቸው። የወቅቱ ወንጀለኞች ዛሬ ተቃዋሚ ነን በሚሉ ድርጅቶች ስርና ዙሪያ የተቃዋሚ ጭምብልን አጥልቀው እንዳሉም መዘንጋት አይገባንም። ከዚህ ባሻገር ግን ቀደም በድንጋይ ዳቦ ዘመን የኢሕአፓ አባሎች የነበሩ ዛሬ ሰልፋቸውን ከሕዝብ ጠላት ቢያደርጉም ተጠያቂው ኢሕአፓ ሊሆን አይችልም። ኢሕአፓ የሚዳኘውና የሚመዘነው ከዕለታት አንድ ቀን አባሎቹ በነበሩና ዛሬ ከህዲ፣ ባንዳ ወይም አንጃ በሆኑት ሳይሆን ዛሬ ባለው አቅዋም፣ አባሎቹና እንቅስቃሴው ነው። የከሀዲ ነገር ከተነሳ ድገሞ ከየድርጅቱ ስንቱ ለጠላት እንዳደረ ሁላችንም የምናውቀው ነው?

ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካና የሀገራችን ወቅታዊ ጥያቄ ሌላ ሲሆን ደግሞ ኢሕአፓ ቂም በቀል ሳይል ፍርድን ለሕዝብ በመተው ከመኢሶንም ጋር ሆነ ሌሎች ጦርነት ካካሄዱበትም ጋር በሀገር አድን ግንባሮች በአንድነት ተሰልፏል፡፡ አዴኃቅ የተባለው ግንባር እንዳይመሰረት የአሜሪካ የሰለ ላ ድርጅት በቅጥረኞቹ አማካይነት ያደረገውን ሻጥርና በዚህም ርኩሰ ተልዕኮ ዛሬ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ነን የሚሉ ግለሰቦች መሳተፋቸውን ኮሞዶር ጣሰው ባፃፉት መፅሀፍ ግልፅ አደርገው ያሰቀመጡት ሀቅ ነው፡፡ ወያኔና ሻዕቢያንም በመደገፍ የኢዴኃቅን ምሰረታ የሻጠሩና ያዘገዩት ከሀዲዎች ራሳቸውን ያውቃሉ፡፡ ኢዴኃቅ የተባለው ግንባር ለሕዝብ ትግል ተገቢውን አስተዋፅዖ አያደረገ ሳለ የደርግ አባል በነበረው አንድ ኮለኔል የተፈፀመበት ደባ ምን ያህል እንደ ጎዳው የሚታወስ ነው፡፡ ኢዴኃቅ ለትግሉ አስተዋፅዖ ሲያደርግ ቆይቶ በኢዴኃን በጊዜው ተተክ ቷል፡፡ ኢዴኀቅ ተቃዋሚ ሀይሎች ልዩነታቸውን በመለስተኛ ደረጃ ይዘው ሊተባባሩና ሊታገሉ እንደሚችሉም ምሳሌ ሆኖ ሚናው ሲያበቃ ያበቃለት ቅንጅት ነበር እንጂ ማንም የሆነ ድርጅት ያፈረሰውአልነበረም፡፦ ወደ ኢዴኃኀ ስንመጣ ደግሞ የዚህን ህብረት የመቋቋም ጥረት አንድ አበደ ውሻ የተቃወሙትን ሁሉ እናውቃቸዋለን፤፤ ህብረቱ አንደተመሰረተም ሊያፈርሱት ተጨባ ጭ እርምጃ የወሰዱት የህብረቱ ተካፋይ የነበሩት ኢዴፓና መኢአድ ለመሆናቸው ምስክር መጥራት አያሰፈልግም፡፡ እነዚህም ከሌሎች አብረው ቅንጅት ከተባሉ በኋላ የተፈጠረውን ሁኔታ ሕዝብ ያውቀዋል፡፡ የ1997 ኡ ምርጫና ከዚያም ተዘጋጅቶ የነቤረው የሕዝብ አድማ እንዴትና በነማን እንደተደናቀፈ፤ ማን ህብረቱን ክዶ ቅንጅትን ክዶ ወደ ወያኔ ፓርላማ አንደገባ ሕዝብ ያውቃል፡፡ያውቃልናም የፍርሻና የመለያየቱን ጉድ በኢሕአፓ ላይ ለመጫን የሚጥሩት ሀሰተኞች ከንቱ ከመሆን ሌላ ማንንም አያደናግሩም፡፡

ኢሕአፓ የትግሉን ትኩረት በማየት በአልባሌ ጥያቄዎች ላይ ማተኮርን ባለመፈለጉ ዝምታን ቢመርጥም አስፈላጊ ከሆነ ለሁሉም ዋሾዎች ምላሽ የመስጠት ችሎታና በቂ መረጃም እንዳለው መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡ ትላንት በሕዝበ ደም የተጨማለቁና ዛሬ ከደሙ ንፁህ ነን ብለው የተቃዋሚ መሪ ነን ሊሉ የሚከጅሉትና አላርፍ ያለች ጣት እንዲሉም በኢሕአፓ ላይ የሚዘምቱ ትን በዝምታ የምናልፍበት ጊዜ እያከተመ ነው፡፡ የአፍራሽነትና በታኝነትን ዛር ያገቡና ቢማሩ ም መሀይምነት አልለቅ ያላቸው ግለሰቦችም በየመደረኩ በኢሕአፓ ላይ ሀሰትን ሲለፍፉ በዝምታ የሚታለፉበትም ጊዜ እያበቃ ነው፡፡ እስከመቼ ይዋሻል ነውና ጥያቄው ቢመከር ቢመከር አልሰማ ላለው ደግሞ በግድ የሚሰማውን ማሰሚያው ጊዜ ደርሷል፡፡ ከዳተኛ ብዙውን ጊዜ ሐሜተኛ ነው ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ክህደታቸው በዝቶ ስብዕናቸው ጥሎአቸው ሄዶ ቢያንኳኳቸው ባዶ በርሚል ሆነው የሚንኳኩ ናቸው፡፡ አስመሳይ ሰዎች፡፡ አስመሳይ ሀገር ወዳዶች፡፡ የእርስዎ የአቶ መለስ ጭንቅላት ከእኛ ከአስር ምሁሮች ይበልጣል ባዮች፡፡ ቅንድብ አድናቂ ማፈሪያዎች፡፡ ዘመናዊ ባንዳዎች፡፡ የውሸት ጮማ ቆራጮች፡፡

ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ እንደተባለው ሁሉ ኢሕአፓ ሀሰተኞችን ንቆ ቢተዋቸውም መፍጨርጨራቸው አላበቃ ስላለና ዛሬ ደግሞ በወያኔ ታጅበው ድርጅቱን ለማስጠላት የተጋጋለ

ዘመቻ ላይ በመሆናቸው ኢሕአፓም አስፈላጊ በሆነው ሁሉ መንገድ ይታገላቸዋል:: ጉሙ ሲቀል የት አባትህ ትገባ አንተ ሌባ ነው ዛሬ ሁኔታው::

**ይቀጥላል**